# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው
ያስነብቡ !
አባዝተው
ያሰራጩ !

የግንቦት 7 ፤የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 16 ነሐሴ 29 2000 ዓ.ም


## አገዛዙ በገንዘብ እጥረትና ጦርነት ውጥረት ውስጥ ገብቷል

በአለፉት 17 አመታት ኢትዮጵያን የገዛው አምባገነኑ የመለስ አገዛዝ በጦርነትና በገንዘብ ቀውስ ውስጥ እንደሚገኝ ምንጮች እያመለከቱ ነው።በውጭ ምንዛሬ እጥረት ፣ በገንዘብ ግሽበትና በተበላሸ አስተዳደር አገሪቱን ከቀን ወደ ቀን ችግር ውስጥ እየከተታት የመጣው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሰሞኑን ደግሞ በረሀብ ለተጠቁ ወገኖች የሚሰጠው እርዳታ በገንዘብ እንዲለወጥለት ጥያቄ ማቅረቡ ብዙዎቹን ሲያነጋግር፣ በሶማሊያ ያደረገው ወረራ የተሳሳተ እንደነበር በተዘዋዋሪ መንገድ እየገለጸና ለመውጣት እያሰበ መሆኑ ታውቋል።ከህዝብ ፍላጎትና ድጋፍ ውጭ በሶማሊያ ላይ ያደረገው ወረራ ፣ ሰራዊቱን ለከፍተኛ ሞትና ስቃይ መዳረግ ብቻ ሳይሆን የአገሪቱን ሀብት በሚሚጠጥ አሁን ለተፈጠረው ችግር አስተዋጽኦ ማድረጉን ባለሙያዎች እየተናገሩ ባሉበት ወቅት ፤በተለይ በሶማሊያ መሪዎች መካከል ስምምነት መጥፋቱ፣ የእስልምና መሪዎች የተለያዩ ከተሞችን እየተቆጣጠሩ መምጣት፣ በኢትዮጵያ የሚታየው የኑሮ ውድነት፣ ረሀብ እና የሰላም መጥፋት አገዛዙ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ እንዲገባ እንዳደረገው እየተገለጸ ነው። አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት የእስልምና ፍርድቤቶች ኪስማዩንና ሌሎች ስትራቴጂክ ጠቀሜታ ያላቸውን ቦታዎች ሲቆጣጠሩ ፣ የኢትዮጵያ ጦር እርምጃ ለመውሰድ አለመቻሉ ድክመቱን የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን፣ ተቃዋሚዎች ሀይላቸውን እንዲያጠናክሩ እየረዳቸው ነው።

ተቃዋሚዎች ምናልባትም የኢትዮጵያ ጦር ሶማሊያን ለቆ ሲወጣ ፣ ሞቃዲሾን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመቆጣጠር ይችላሉ ተብሎ ይገመታል። ይህ ከሆነ ደግሞ የሶማሊያ ጦርነት ምንም ውጤት ሳያመጣ፣ በአንጻሩ አገሪቱን ለችግር ዳርጓት ሊያበቃ ይችላል ማለት ነው ይላሉ አስተያየት ሰጭዎች።እንደነዚህ ሰዎች አባባል፣ የሶማሊያም ጦርነት እንደባድሜ ጦርነት ውጤት አልባ መሆን ብቻ ሳይሆን ለረጅም ጊዜ የኢትዮጵያ ችግር ሆኖ ሊዘልቅ ይችላል።
አምባገነኑ መለስ፣ ሰሞኑን ለአለማቀፍ የመገናኛ ድርጅቶች በሰጣቸው ቃለምልልሶች፣ በሶማሊያ የሚያደርገው ጦርነት አገሪቱን ለብዙ ወጪ እንደዳረጋት አምኖአል።በተለይም የአለማቀፍ የመገናኛ ድርጅቶች መለስ ዜናዊ ህዝቡን እያስራበና እርዳታ እየለመነ፣ በጎን ደግሞ እጅግ አባካኝ የሆነ ጦርነት ያካሂዳል የሚል ትችት በማቅረባቸው፣ አገዛዙ መደናገጡን ምንጮች ሲገልጹ፣በተቻለ መጠን ይህ ጦርነት በፍጥነት እንዲያልቅ ፍለጎት ያለው መሆኑን ሰሞኑን በአዲስአበባ ለሽምግልና ተቀምጠው ለነበሩት የሶማሊያ ፕሬዝዳንትና ጠቅላይ ሚንስትር እንደተገለጻቸው ምንጮቻችን ጠቁመዋል።

በተያያዘ ዜና የመለስ አገዛዝ በኦጋዴን የሚገኙ ዜጎችን እንዲሁም በፊት ቅንጅትን ይደግፉሉ ብሎ ለጠረጠራቸው ሰዎች ሁሉ እርዳታ እንዳያገኙ እያደረገና በረሀብ እየቀጣቸው መሆኑን ከስፍራው የሚደርሱን ዘገባዎች ያመለክታሉ።በኦጋዴን ያለው ሁኔታ ሰሞኑን ወደ ስፍራው ለጉብኝት የተጓዙትን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ተወካይ ጭምር ያስቆጣ ሲሆን፣ ከፖለቲካ እምነታቸው ጋር በተያያዘ እርዳታ የተከለከሉትን ዜጎች ግን የሚያስታውሳቸው ድርጅት መጥፋቱን ምንጮች ተናግረዋል።

## የኢህአዴግ ጉባኤ ሀገሪቷን ወደ አንድ ፓርቲ ስርአትነት የሚያሸጋግሩ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል ተብሎ ይጠበቃል

በዚህ ሳምንት ይደረጋል እንደሚደረግ የሚጠበቀው 7ኛ የኢህአዴግ ድርጅታዊ ጉባኤ ድርጅቱ የሃገሪቱን የፖለቲካ መድረክ በሙሉ እንዲቆጣጠር ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩ ውሳኔዎችን እንደሚያስተላልፍ ተገለጽ።ይህ የተገለጽው ለጉባኤው ሊቀርብ የተዘጋጀን ሰነድ የተመለከቱ ታዛቢዎች አስተያየት መነሻ በማድረግ ነው።በዚህ መነሻነት ረቂቅ አጀንዳው የግንባሩ ጉባኤ የሃገሪቷን ፖለቲካ ሜዳ በሙሉ ለኢህአዴግ የሞኖፖል ጨዋታ የሚያመቻቹ ብዙ የውሳኔ፣
ወደ ገጽ 2 ዞሯል

## በመሃል አዲስ አበባ በፍንዳታ ጉዳት ደረሰ

ትላንት ከቀትር በሁዋላ አውቶቢስ ተራ ተብሎ በሚጠራው ጠከተማይቱ ክፍል የደረሰ ፍንዳታ የህይወትና የአካል ጉዳት ማድረሱን የሆስፒታል ምንጮች ገለጹ።በአንድ የወጣቶች መዝናኛ ስፍራ ላይ በደረሰው በዙህ አደጋ የሞቱና የቆሰሉ እንዳሉ ሲታወቅ፣ሰለባዎች በተለያዩ የከተማይቱ ሆስፒታሎች ሲረዱ እንደነበር ታውቋል።የሰውነታቸው አካል የተጎዳ ሰለባዎችን መመልከቷን የገለጽች አንድ ታዛቢ ከቀላል እስከ ከባድ የሚባል ጉዳት መድረሱብ የአይን እማኝነቷን ገልጻለች።
ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባልተለመደ ሁኔታ በአዲስ አበባ የተለያዮ ጊዜያት የቦምብ ፍንዳታዎች መድረሱ ሲታወቅ፣ከዚህ ቀደምቶቹ በቤንዚን ማደያና የትራንስፖርት ሚኒ ባሶች ላይ ያነጣጠሩ የነበሩ ሲሆን፣በዚህኛው ጥቃት የወጣቶችን መሰብሰቢያ ኢላማ ማድረጉ ብዙዎችን አሳደንግጧል።በከተማው የሚሰራጩ የኤፍ-ኤም ሬዲዮኖች ዜናውን ካሰራጩ ጅምሮ በከተማዋ የተለያዮ ክፍሎች የመንግስት ጸጥታ ሃይሎች ፍተሻዎችን ማድረጋቸውን ለማወቅ ችለናል።ለእስካሁኖቹም ሆነ፣ለዚህኛው ጥቃት ሃላፊነቱን እወስዳለሁ ያለ አካል አልተገኘም።በንጹሃን ዜጎች ላይ የሚፈጸመው ይህ ጥቃት አላማው ምንም ሆነ ምን ተገቢ ባይሆንም፣ምናልባት ስርአቱ ከፈጸማቸው የሃገር ውስጥና የውጭ ፖሊሲ ስህተቶች ጋር እንደሚያስተሳስሩት በጉዳዩ ላይ አስተያየት የሰጡ የፖለቲካ ተንታኞች ገልጸውልናል።

### የግንቦት 7 ንቅናቄ አጭር ሞገድ ሬድዮ ስርጭት

### መስከረም 1፣ 2001 ዓም ይጀመራል

ግንቦት 7 ለፍትህ፣ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ በሳምንት ሶስት ቀናት ማለትም
ማክሰኞ፣ሐሙስና ቅዳሜ ከምሽቱ 2፡00 እስከ 2፡30 ፤ በ17655 ኪሎ ኸርዝ በ16 ሜትር ባንድ ወይም በ21555 ኪሎ ኸርዝ በ13 ሜትር ባንድ ወደ ኢትዮጵያና ሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚያሰተላልፈውን የሬዲዮ ፕሮግራም

## ርእሰ አንቀጽ

## የግንቦት ሰባት ድምፅ

## ድምፃቸው ለታፈነ ልሳን ለመሆን

ልክ የዛሬ ሳምንት፤ መስከረም 1 ቀን 2001 አም፤ የግንቦት ሰባት ድምፅ በመላ የሃገሪቱ ማእዘናት የኢትዮጵያን ጩኸት ያሰማል። የኢትዮጵያን ዋይታ ያስተጋባል። የኢትዮጵያችንን ተስፋ ይፈነጥቃል። ለታፈኑ ድምፅ ለመሆን ፤ ለተጋዙ በአለኝታነት ፤ ለታሰሩ ብርሃን ፤ ለሚታገሉ ሁሉ ደግሞ ተጨማሪ አቅምን ለማዋስ። የታጋዮች ሁሉ የጋራ መድረክ ለመሆን አቅዶ የተነሳ ድምፅ ነው ። ባለፈ አለመግባባት፤ ወይም መለያየት፤ በጊዜያዊ የትግል አቅጣጫ ልዩነት ላይ አያተኩርም። እንዲያውም እነዚህ ሁሉ ፀረ-እብሪተኝነት ሃይሎች ያተኮሩበትን አላማ ከግብ ለማድረስ የቆሙ ስለሆነ፤ የሁሉንም ትግል እንደራሱ በመውሰድ፤ በታላቅ የሃላፊነት ስሜት ያስተዋውቃል፤ የትግል ጥሪዎቻቸውን ያሰማል፤ እንግልታቸውን በየደቂቃው እየተከታተለ ፤ የጉዳዩ ባለቤት ለሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ይናኛል።

ህዝባችን በግንቦት 97 የፈነጠቀውን አቅሙን ለማዳበር፤ የህዝባዊ ሥርአት ተስፋውን ለመጨበጥ ቆርጦ እንዲታገልና፤ በተስፋ መቁረጥና ፍርሃት ከአውዳሚ መንግስታዊ ሃይሎች ጋር እንዳይተባበር ያነሳሳል። የመለስ እብሪተኛ አገዛዝ በጦር ሃይሉ በመመካት ያዳፈነውን ሚዲያ በአዲስ አበባ ክልል ከተቀየደ የህትመት አገልግሎቱ በላቀ መንገድ፤ ከባድመ እሰከ ሞያሌ ፤ ከአሶሳ እስከ ገናሌ ድረስ ያሉትን ጎጆዎች በር ሁሉ ያንኳኳል። ኑ ! መነጣጠልን ፤ ጥላቻን ፤ ፍርሃትን ፤ ለባለሥልጣን ማጎንበስን ፤ ጠባብ ብሂርተኝነትን ፤ ትምክህትን ፤ እብሪትን አስወገዱ ፤ ከመጥፎ ልማዶች ፅዱ ፤ ከጫትና አደንዛዥ እፅ ፤ ከመጠጥና ሃሜት ፤ ከተስፋ መቁረጥና ጨለምተኝነት ውጡ፤ አዲሲቱን ኢትዮጵያ በፍላጎታችሁ ብርሃን አምጣችሁ ውለዷት እያለ ያስተባብራል ።

ነብሳቸውን ለ170 ካሬ ሜትር ወለድ አገድ አስይዘው በፍርሃት ከሚርዱ ስደተኞች በቀር ፤ የተቀሩትን ምሁራን ሁሉ እየጋበዘ ፤ በሃገራቸው የተነፈጉትን መድረክ እንዲያገኙ ያደርጋል ። ከህዝባቸው እንዲመክሩ መረብ ይዘረጋል ። እነዚህ ሁሉ ታላቅ እሳቤዎች ናቸው ። ለደጉ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚመጥኑም ናቸው ። በጥቂት የግንቦት ሰባት ንቅናቄ አባላት ድካም ብቻ ግን ከታለመላቸው ግብ ይደርሳሉ ማለት አይደለም ። ፈረሱም ሜዳውም ይሄው ብለናል ። የለውጥ ሃይሎችና መላው ህዝባችን ግን የግንቦት ሰባት ድምፅን እንደ ዐይኑ ብሌን ተንከባክቦ ካላሳደጋት ልትጠወልግ ትችላለች ። መረጃ በመላክ ፤ ዜና በማቀበል ፤ በሥራ ገበታ ላይ የተገኙ ምስጢሮችን በማስተላለፍ ፤ ወዘተ ሁሉም ዜጋ ለዚህ ታላቅ ትልም ስኬታማነት አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላል ። ይጠበቅበታልም ። የመረጃው አይነት ዘርፈ ብዙ ነው ። አንድ የህንፃ ተቋራጭ ስለተጀመረው ህንፃ ባለቤት ማንነት መረጃ ሊልክ ይችላል ፤ የባንኩ ክለርክ ደግሞ የብድሩን መጠን ፡ የማዘጋጃ ቤቱ ሰራተኛ ደግሞ መሬቱ እንዴት እንደተገኘ መረጃ ሊልክ ይችላል ። እነዚህ ሁሉ ተናጠል መረጃዎች ወደ አንድ ማእከል ደርሰው ሲገጣጠሙ ፤ ትክክለኛው ስእል ይገኛል ። የጥናትና ምርምር ክፍላችን የደረሰበትን መደምደሚያ ደግሞ ለሬዲዮ ዝግጅታችን ሲልክ፤ ህዝባችን በንብረቱ በህይወቱና በሃገሩ የሚነግዱት ሃይሎች እነማን እንደሆኑና፤ እንዴትስ ጥሪቱንና ተስፋውን እያሟጠጡት እንደሆነ ግልፅ ይሆንለታል ። መረጃ ሃይል ነው ። በመረጃ የታጠቀ ህዝብ ደግሞ የአላማ ጥራትና ጽናት ይኖረዋል፡፡ የሚነሳበትንና የሚደርስበትን ያውቃል፡፡ ለነጻነት፣ ለመብት፣ ከድህነት ለመላቀቅና ሃገርን ለመታደግ ቆርጦ በተነሳ ህዝብ ፊት እንኳን ውስጡ ተቦርቡሮ ያለቀ የመለስ አምባገነናዊ አገዛዝ ቀርቶ ከመለስ በላይም ሰላይና ገዳይ፣ ጥይትና ቦንብ የነበራቸውም ሃያሎችም መቆም እንዳልቻሉ ይረዳል፡፡ ህዝብን በመረጃ ማስታጠቅ የአምባገነኖችን ትጥቅ ማስፈቻው አንዱ መንገድ ነው፡፡ የግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሴ ንቅናቄ አምባገነኖችን መወጋት የሚቻልባቸውን የትግል ዘርፎች በሙሉ ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ የግንቦት ሰባት ድምፅም ታላቅ ሥነ-ልቡናዊና ህሊናዊ ሀይል እንደሚሆን ተስፋችን የላቀ ነው ። የህዝባችን እገዛ ሲጨመርበት ደግሞ ከተስፋም አልፎ ምድራዊ ሃይል ወደመሆን ይለወጣል ። የነገ ሰው ይበለን ።

### የኢ.ህአዴግ ጉባኤ ህገሪቷን ከገጽ 1 የዞረ

ሃሳቦችን እንደሚያስተላልፍ ተጠብቋል።በዚህም መሰረት ከኢ.ህአዴግ ፍላጎት ውጭ ለስርአቱ ስጋት በመፍጠር ላይ ያሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን በትክክለኛው መስመር እንዲሄዱ ካልሆነም የሚያወላውሉትን በህግና አስተዳደራዊ እርምጃ ለመቅጣት መታቀዱን፣ በተጨማሪም አደገኛ የሆነ እንቅስቃሴ ውስጥ የገቡና የመግባት አዝማሚያ ያላቸውንም ተቃዋሚዎችን ጨርሶ ለማጥፋት እንደሚሰራ በሰነዱ ላይ አስፍሯል።ከምርጫ 97 ትምህርት በመውሰድ ማንኛውንም የተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ አቃሎ መመልከት እንደማይገባና በቅርብ የሚሰሩትን መከታተል ያስፈልጋል ሲል ኢ.ህአዴግ በሰነዱ አስፍሮአል።ከአሁን በሁዋላ በምርጫ ወቅት አላስፈላጊ የሆኑ የተቃዋሚዎች ተግባራትን ከምርጫ ቦርድና የህግ አካላት ጋር በመተባበር በማስቆም አደጋው እንዳይከሰት መካላከል እንደሚያሻ ኢ.ህአዴግ አትቷል።

በህብረተሰቡ ውስጥ የአብዮታዊ ዴሞክራሲን አስተሳሰብ ለማስረጽ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ካድሬዎችን ለማሰልጠን የተሞከረ ሲሆን፣ወደፊትም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን አባላት በግንባሩ ማሰልጠኛ ለማሰልጠን መታቀዱን ረቂቁ ገልጿል።ወደ 4.5 ሚለዮን የሚጠጉ አባላት አሉኝ የሚለው ኢ.ህአዴግ በመላ ሃገሪቱ በመሰረታዊ ድርጅቶችና የጥናት ህዋሳት ስር የተዋቀሩ አባላቱን በማሰማራት ህብረተሰቡን መቆጣጠርና ለፓርቲው ታዛዥ ማድረግ እንደሚገባ በዚህ ረቂቅ ያፋ አድርጓል።

ይህው የኢ.ህአዴግ ድርጅታዊ ጉባኤ ረቂቅ ሪፖርት አሁንም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ነጻውን ፕሬስ በጠላትነት የፈረጀ ሲሆን፣እነዚህን አካላት ለመቆጣጠርና ለማጥፋት ያልተሰሩ ተግባርት እንዳሉ ገልጾአል፣በሚያስገርም ሁኔታ ኪራይ ሰብሳቢ የሚል ተቀጽላም ሰጥቶአቸዋል።ነጻ-ፕሬስን በተመለከተ ከምርጫ 97 በሁዋላ የታዩ አንዳንድ አስጊ አዝማሚያ ያላቸው ላይ እርምጃ የተወሰደ ሲሆን ቀደም ሲል በሚዲያው ላይ አፍራሽ አዥማሚያ የነበረው ሃይል ወደ ሚዲያው እንዳይመለስ ማድረግ አለብን ብሏል።የኢ.ህአዴግ ጉባኤ ላይ አዲስ የአመራር አባላት ወደአመራሩ እንደሚመጡ ሲጠበቅ፣ለሚቀጥሉት አመታት ድርጅቱን የሚመሩ የአመራር አባላት ሽግሽግ እንደሚኖር ተገምቷል።ከዚህ በተጨምሪም በዚህ ጉባኤ የኢትዮ-ኤርትራ ድንበር ጉዳይ ላይ ውሳኔ ይሰጣል ተብሎ እንደሚጠበቅ ተንታኞች ተናግረዋል።

## የጥበብ አንቀጽ

### ይድረስ ለታጋዩ

ወይራ መሆንህን-
ላ'ፍታ ካልዘነጋህ፣
ታውቃለህ መከራህ-
እንደሆነ ፀጋህ።
ፀንተህ ቁም ሲወቅጡህ-
ሲበዛ ቅጥቀጣህ፣
ያኔ ነው ለመቅረዝ-
ዘይት የሚወጣህ።

ግንቦት 7 ድምጽ በግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

# የፖለቲካ ትንትና

በዚህ አምድ ስር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ መጣጥፎች ይቀርባሉ

**የግንቦት7** የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ

## የግንቦት7 ድምጽ ራድዮ ፕሮግራም መስከረም 1፤2001 ዓ.ም ይጀመራል።

በአገራችን ላይ የተንሰራፋው አምባገነናዊ አገዛዝ፣ ግፈኛ ስርአቱን ማራዘም ከሚችልባቸው መሳሪያዎች አንዱ ህዝብ ስለሃገሩ አጠቃላይ ሁኔታ በቂ መረጃ እንዳያገኝ፣ በእዚህ መረጃ አማካይነት እርስ በርሱ ተገናኝቶ እንዳይመክር፣ መክሮም አስከፊ ህይወቱን ለመቀየር በጋራ እንዳይነሳ በማድረግ ነው፡፡ ባለፉት 17 አመታት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የሃገሪቱን የመገናኛ ብዙሃን በተለይ ብዙሃኑን በቀላሉ መድረስ የሚችሉትን፣ ራድዮና ቴሌቪዥን በሞኖፖል ይዞ፣ በአፍሪካ ውስጥ እንኳን የሚታየውን የሚድያ ነጻነት የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳይጎናጸፍ አፍኖ የያዘበት ምክንያት ህዝብ ከነጻ ሚድያ በሚያገኘው መረጃ ከታጠቀ፣ ለመብቱና ለጥቅሙ እንደሚነሳ በመፍራት ነው፡፡ በእዚህ ታፍኖ ያለተቀናቃኝ በተያዘ ራድዮና ቴሌቪዥን ቀንና ማታ በሬ ወለደና ሌሎችንም ተመሳሳይ ውሸቶች ሲቀድበት፣ ረሃብን ጥጋብ አድርጎ ሲያቀረብበት፣ ድህነትንና የኑሮ ውድነትን እንደ የኢኮኖሚ እድገት እዩልኝ ሲልበት፣ የሃገር ክህደት እየፈጸመ መልካም ጉርብትና የሚል ስም እየሰጠ ሲያላገጥበት፣ ዘረኛ ከፋፋይነትን እያስፋፋ፣ መብት አስከብሬ ያመጣሁት አንድነት እያለ ሲያሾፍበት፣ ራሱ አጭበርብሮና ገሎ የተጭበረበረውንና የሞተውን ህዝብ መልሶ ሲወነጅልበት አይተናል፡፡

80 ሚሊዮን የሚጠጋው ህዝባችን የራሱ ሀብት በሆኑት የመገናኛ ብዙሃን ተቋሞች ሃሰቡን እንዳይገልጽ ታግዶ፣ የመናገር መብት የተሰጣቸው እፍኝ የማይሞሉ የስርአቱ ምርጥ ልጆች የሆኑበትና በአደንቋሪ ፕሮፓጋንዳቸው ህዝብን ያስመረሩበት ሁኔታ በሃገራችን እንደነገሰ ነው፡፡ በመጠኑም ቢሆን ለተወሰኑ አካባቢዎች የተለያዩ አስተሣሰቦችን ሲያቀርቡ የነበሩ የግል ፕሬሶችም፤ የግንቦት 1997 ዓ.ም ምርጫን ተከትሎ እንዲጠፉ ተደርገዋል። ከሁለት ዓመት እስር በሁዋላ ከተፈቱት ጋዜጠኞች መካከል አንዳንደቹ በወከባ መብዛት አገራቸውን ጥለው ተሰደዋል፣ አንዳንዶቹ ዳግም ጋዜጣ በማሳተም ሥራ ለመሰማራት ጠይቀው ተከልክለዋል፡፡ በአዲስ መልክ የጀመሩ ጥቂት ጋዜጦችም በአደጋ ውስጥ ይገኛሉ። ከዚያም ባሻገር የተለያዩ አስተሣሰቦች የሚንሸራሸሩባቸው ኢትዮጵያዊ ድረ-ገፆች ለኢትዮጵያ ህዝብ እንዳይደርሱ ታግደዋል። ይባስ ብሎ በአዲስ አፋኝና ጨቋኝ ህግ ከለላ፤ በሃገሪቱ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ የመብት ጭላንጭል ለአንዴና ለመጨረሻው ለማዳፈን ቆርጦ ተነስቷል፡፡በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ ውስጥ ነው፣ አምባገነናዊነትን ወደ ታሪክ ትቢያነት ለመለወጥ የተነሳው የግንቦት 7 ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ፤ በሣምንት አንድ ቀን ከሚያዘጋጀው ጋዜጣ በተጨማሪ፤ በአዲሱ ዓመት ነጻነት ለተጠማው የኢትዮጵያ ህዝብ አዲስ የተስፋ ስጦታ ለማቅረብ ዝግጅቱን ያጠናቀቀው።

"መረጃ ሃይል ነው፡፡ በመረጃ የታጠቀ ህዝብ ለመብቱ፣ ለነጻነቱ፣ ለጥቅሙና ለሃገሩ ደህንነት የቆረጠ ታጋይ ይሆናል" ከሚል እምነት በመነሳት፤ ንቅናቄያችን በሳምንት ሶስት ቀናት ማለትም ማክሰኞ፣ ሐሙስና ቅዳሜ ከምሽቱ 2፡00 እስከ 2፡30 ፤ በ17655 ኪሎ ኸርዝ በ16 ሜትር ባንድ ወይም በ21555 ኪሎ ኸርዝ በ13 ሜትር ባንድ ወደ ኢትዮጵያና ሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚያሰተላልፈውን የሬዲዮ ፕሮግራም መስከረም 1 ቀን 2001 ዓ.ም ሐሙስ ምሽት ይጀምራል።ፕሮግራሙ ከአማርኛ ቋንቋ በተጨማሪ ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ በኦሮሚኛና ትግርኛ ቋንቋዎች ስርጭቱን ያቀርባል።በተጨማሪም ፕሮግራሞቹን ከግንቦት 7 ድረ-ገጽ ላይ በመጫን ማዳመጥ የሚቻልበት ሁኔታም መመቻቸቱን እንገልጻለን።

**የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ**

## አደራችሁን ግንቦት ሰባቶች..

ከገጽ 4 የዞረ

ህገ መንግስታዊ መብታችን ነው እንሰበሰባለን አላላችሁም?፡፡ ለመሆኑ በሚቀጥለውና እየደረሰ ባለው የ2002 ዓም ሃገራዊ ምርጫ ላይ ምን እያሰባችሁ ነው?፡፡ ቀደም ብላችሁ የህዝብ መብት የሚያስከብሩ፣ በምርጫ የሚሰጠውን ድምጽ በሚገባ ቆጥረው ስልጣን በደምጽ ብልጫ አሸናፊ ለሆነው ወገን ማስረከብ የሚችሉ ተቋማት ይፈጠሩ፣ ህዝብም ለዚህ መሳካት ከጎናችን ይቁም ብላችሁ፣ ህዝብም በሽዎች ከጎናችሁ ቆሞ ውድ ህይወቱን ሰጥቷል፡፡ በመቶ ሽህ የሚቆጠረው ታስሯል። ተፈናቅሏል። ተሰዷል፡፡ እናንተም በእዚህ አቋም ለሁለት አመት በሃሰት ክስ ታስራችኋል፡፡ ዛሬ ግን ስለእነዚህ ተቋማት ጉዳይ ቃል አትተነፍሱም፡፡ እነዚህ ተቋማት በምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ፣ ችግሩ ተፈቷል? ወይስ ችግሩ እንዳለ ነው ካለ ለምን በእዚህ አጅግ ወሳኝ ነው ብላችሁ ለህዝብ በአንድ ወቅት በገለጻችሁት ጉዳይ ላይ ዝምታን መረጣችሁ እነዚህና ሌሎች ግለሰቡንና የሚወክሉትን ድርጅት በሚመለከት ጥያቄዎች ማንሳት ሲገባ ቃለ ምልልሱ ተጀምሮ ያለቀው ግንቦት ሰባትንና ሌሎችም የመለስን ጥጋብ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ማስተንፈስ ይገባል በማለት አምረው በተነሱት ላይ ሆኖ አይተነዋል፡፡ ግራ የገባን፣ እኔና ጓደኞቼን፣ አላማው ምን እንደሆነ ማወቅ ነው፡፡ ጋዜጣውም ተጠያቂውን ዋናውን ነፍሰ ገዳይ፣ አፋኝ፣ ሰው ገፊ፣ ትተው አላማቸው በእዚህ ግፈኛ መንግስት ተገፍተው ያለፍላጎታቸው ከሃገራቸውና ከቤታቸው ተፈናቅለው በዱር በገደሉ በሰው ሃገር በስደት በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ላይ መሆኑ አስደንቆናል፡፡ ይህንን ሁሉ የዘበዘብኩት የታዘብናቸው መሆኑን እንዲያውቁት እንጂ እናንተ እንደኔ ጊዜያችሁን በእዚህ ጉዳይ እንድታጠፉ አይደለም፡፡ እንዲያውም በመሃከሉ እየተብከነከንኩ እረሳሁት እንጂ አደራ የምላችሁ ይህንኑ ነው፡፡

ድፍን ኢትዮጵያ እንደ መለስ አገዛዝ የሰለቸውና የመረረው በአንድነት የማይቆሙ፣ ዋናውን ጸረ- ህዝብና ጸረ ሃገር ቡድን አስቀምጠው እርስ በርሳቸው ሲሰዳደቡ፣ ሲናቆሩ፣ የመከራ ግዜያችንን የሚያራዝሙ ተቃዋሚዎችን መስማት ነው፡፡ ግለሰቦች መረን ያለፈ ነገር ተናገሩን ብላችሁ ብዙ ስራ መስራት የሚችል ብእራችሁንና ግዜያችሁን በከንቱ እንዳታጠፉ ለማሳሰብ ነው፡፡ ሁሉን ነገር፣ ሁሉን በሚገባ ለመመዘን በቂ ችሎታ ላለው፣ ደጋግማችሁ እንደምትሉት ለምትተማመኑበት ህዝብ ትታችሁ ወናው ትኩረታችሁ በመለስ ዜናዊ አረመኔያዊ አገዛዝ ላይ ብቻ ያነጣጠረ ይሁን፡፡ ስራ ፈተው ስራ ሊያስፈቱ ለሚፈልጉ ቡድኖችና ግለሰቦች ትንኮሳ መልስ አትስጡ፡፡እንደ እውነቱ ከሆነ በሃገር ቤት ያለውን ተቃዋሚ ደግሞ በማይረባ ነገር የተጠመዱ ጥቂት ግለሰቦች አይገልጹትም፡፡ አብዛኛው ተቃዋሚ ድርጅትና ደጋፊዎቹ በራሳቸው መንገድ የራሳቸውን ትግል በማድረግ ከእዚህ አፋኝ ስርአት ሁላችንም እንድንገላገል የራሳቸውን፣ ትንሽም ብትሆን ጥረት የሚያደርጉ ስለሆኑ ወገን እንጂ ጠላት አይደሉም፡፡ ደግሜ እጠይቃለሁ ትኩረታችሁን፣ የምታነጣትሩት በአገዛዙ ላይ ብቻ ይሁን፡፡ ሌላውን ለዘመንና ለህዝብ ፍርድ ተውት፡፡ መልሳችሁን እጠብቃለሁ፡፡

## ከግንቦት 7 የህዝብ ግንኙነት ክፍል የተሰጠ ምላሽ

ውድ አቶ ታየ ተግባሩ፣ማሳሰቢያዎን አድምጠናል፡፡ የእኛም ፖሊሲ ይኸው ነው፡፡ የጠየቁንን ቃል ኪዳን በአደባባይ ለመግባት አንቸገርም፡፡ ሁሌም ትኩረታችን በአምባገነኑ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ ነው፣ ወደፊትም በእዚሁ እንቀጥላለን፡፡

# ሃይለ ሀሳብ

በዚህ አምድ ስር የተለያዩ ነጻነትንና ትግልን የተመለከቱ ጉዳዮች ይስተናገዳሉ

## አደራችሁን ግንቦት ሰባቶች!!

ታዬ ተግባሩ ከአዲስ አበባ

ጉዳዩ እንደዚህ ነው፡፡ እዚህ የምንገኝ ወገኖቻችሁ ግማሾቻችንን እረሃብ ይፈጀናል፡፡ ግማሾቻችን ካቅማችን በላይ የሆነ የኑሮ ውድነት ከሚራቡት ጎራ ቀላቅሎናል፡፡ አብዛኛው የሃገሪቱ ሰው የማያውቀው፣ ሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች ጆሮ የማይደርሰው አፈና ብዙ ነው፡፡ እንደወጡ የሚቀሩ፣ የት እንደደረሱ የማይታወቁ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ ተወስደው በህጋዊ እስር ቤት ሳይቀርቡ ከአንድና ከሁለት ወራት በላይ ሲቀጠቀጡ ቆይተው የት እንደነበሩ እንዳያውቁ አይናቸውን በጥቁር ጨርቅ ተሸብበው የትም ሜዳ ላይ በጭለማ ከሚኪና ተወርውረው የሚጣሉ አሉ፡፡ በገዛ ጓደኛዬ ላይ ባይደርስ ወሬ ነው እል ነበር፡፡ ከቤቱ እንደወጣ ከቀረ ከአንድ ወር በኋላ አጽም መስሎ መከሰቱን በአይኔ አይቻለሁ፡፡ በጆሮው የተናገረውን ስለሰማሁ ነው የምጽፈው፡፡ የሚታሰረው በሃሰተኛ ዳኛ የግፍ ፍርድ የሚፈረድበት፣ የሚታፈነው በሙሉ የሃገሩ ጉዳይ የሚያንገበግበው እየተመረጠ ነው፡፡ ስለአገዛዙ ዘረኛነት፣ ሃገሩን አንዴት በጥቂት የማፍያ ቡድን እጅ ይዘው እንደሚዘርፉት፣ ዳር ድንበራችንን እንደ ዳቦ እየቆረሱ ለባእዳን እንደሚያድሉት፣ ወገኖቻችን በማያውቁትና በማያገባቸው ሶማሊያ ወስደው በሀገ- ወጥ ድርጊቸው ስለሚያስፈጁት እውር እብሪተኞች፣ ህዝብ ሰለመራቡ ሚድያው ረሃቡን ለመሸፈን መዋሸቱን፣ ቴዲ የታሰረው ሃገሩን፣ አረንጓዴ ቢጫ፣ ቀይ ባንዲራውን፣ ህዝቡን ስለሚወድ ነው፣ ስለዳኘነት መራከስ፣ ከአጋዛዙ ጋር ተጣብቆ አገርና ህዘብን የሚመጠውን ሆዳም ብሎ መጥራትና መናገር ይህና ሌላውም ተራ ጉዳይ ሳይቀር የመታፈኛና የመቀጥቀጫ ምክንያት ነው፡፡ ደግሞ ቅጥቀጣውን የሚያካሂደውን መለየት አይቻልም፡፡ መለስ ዜናዊና ባልደረቦቹ በህጋዊ ሰላዩ ስር ህገወጥ የራሳቸው ሰላዮች፣ በህጋዊው መከላከያ ሃይል ስር ልዩ ህገወጥ የራሳቸውን የተደራጀ ቡድን፣ በፖሊሱም በፌደራሉም ውሰጥ በተመሳሳይ ያደራጁት አፋኝና ገዳይ ቡድን እንዳለ ግልጽ ነው፡፡ በቀደም በቴሌቪዠን የሚሰራጨውን የቅጥፈት ፕሮፓጋንዳ መስማት የመረራቸው አዛውንት የቡና ቤቲቱን ሰራተኛ ምን አለ ይህን ነገርሽን ብታጠፊልኝ ብለው በመናገራቸው የደረሰባቸውን አበሳ አይቻለሁ፡፡ የአገዛዙ ሁለት ሰላዮች ከመሸተኛው መሃል ነበሩና ተነስተው በሽጉጥ አፋቸውን ቢሏቸው ሁለት ጥርሳቸው እፊታችን ረገፈ፡፡ የሰውየውን የእድሜ በለጸጋነት ተመልክተው በግልምጫ ሊያልፏቸው ይችሉ ነበር፡፡ደግሞ የብልግና ስድባቸው፣ ዘረኛ ስድነታቸው ጉድ እኮ ነው፡፡ አቅም የሌላቸውን ሽማግሌ እንዲያ ሲቀጠቅጡ ማየት ወይ ሃገሬ የሚያሳኝ ነበር፡፡ የጀመርኩት ለስላሳ አፌ ላይ ሬት ሆነብኝ፡፡ይህ እየሆነ ነው በጋዜጣ ላይ ስለግንቦት7 ተጻፈ ተብሎ ዴሞክራሲ አለ ይባልልኛል፡፡ ድንቄም ዴሞክራሲ፣ በየመስሪያ ቤቱ፣ በየቡና ቤቱ፣ በየገበያ አፉን ዘግቶ ተገላምጦ የሚናገረው ህዝብ፣ ዴሞክራሲ በሽበሽ ስለሆነ ነው? እረ ተውኝ፡፡ ዋናው አፈና እኮ የሚካሄደው አለምአቀፍ ማህበረሰቡ በሚያየው መድረክ ላይ እኮ አይደለም፡፡ አለም ማንነታቸውን የሚያውቃቸው ግለሰቦች ዛሬም አንዳንድ ጸረ አገዛዝ የሆነ ነገር ቢናገሩ ምንም ላይሆኑ ይችላሉ፡፡እንደ እውነቱማ ከሆነ ከግንቦቱ ምርጫ ጋር ተያይዞ በመጣው ችግር ማነው የሞተው፣ የተቀጠቀጠው ጸጉሩን ሰላሳና አርባ እየሆነ በአንድ ምላጭ እንዲላጭ እየተገደደ የኤድስ በሽታ ሰላባ የተደረገው፡፡ አገዛዙ የሚበረታው በኔና እኔን በመሰለው ስም የሌለው አለምአቀፍ ማህበሰቡ መፈጠራችንን በማያውቀው ተራ ዜጎች ላይ እንጂ ሌሎችማ ቴሌቪዠን ዝግሉኝ ከሚል ነገር በላይ መንግስትን እየተናገሩ ጸጉራቸው ሳይነካ እቤታቸው ገብተው ያድሩ የለም፡፡ የዴሞክራሲ መለኪያ አገዛዙ ለራሱ አለማቀፋዊ ተቀባይነት ለጥቂቶች በፍላጎቱ የለቀቃት ዴሞክራሲ ቀዳዳ ሆና ከታየች የሚያሳዝን ነው፡፡ብቻ የምናየውና የምንሰማው ብዙ ነው፡፡እናንተም ታውቁታላችሁ ምኑን ነው የምነግራችሁ፡፡ ወይ ጉድ ማልቀስ መጀመርና መጻፍ ለካ አንድ ነው፡፡ አንዴ ከጀመሩት ማቆም አይቻልም ለካ፡፡

ጀማሪ ጸሃፊ ስለሆንኩ ይቅርታ አድርጉልኝ የተነሳሁበትን ረሳሁዋ፡፡ ግንቦት ሰባቶች ዋናው ቁም ነገር የሚከተለው ነው፡፡ እዚህ እናንተ ሁላችንንም ከላንበት ሲኦል ለማውጣት የጀመራችሁትን ትግል ትታችሁ ግዜያችሁን በጉንጭ አልፋ ትግል እንድታጠፉ ስራዬ ብለው የተያያዙትን ተግባር እያየን ነው፡፡ መድረክ ባገኙ ቁጥር፣ ይህችን ምድር ለህዝቦቿ ሲኦል ያደረገውን፣ ብርቅና ድንቅ የሆኑትን ልጆቿን የሚቀጥፈውን፣ የቀሩት የሚወዷትን ሃገር ጥለው እንዲሰደዱ የሚደርገውን፣ ራሳቸውንም ሳይቀር አስሮ፣ የውሸት ክስ ከሶ፣ አስገድዶ ይቅርታ እንዲጠይቁ ያደረጋቸውን ግፈኛ አገዛዝ መታገሉን ትተው ግንቦት ሰባት እንደዚህ ነው፣ አገዛዙን በአመጽ ለመጣል የሚታገሉ ሃይሎች እንደእዚህ ናቸው የሚል ፍሬ ከርስኪ አባባል ሲሰነዝሩ እንሰማለን፡፡ የመለስ አገዛዝ አንዱን ከሌላው ለይቶ ለምን እንደሚያጠቃ፣ ለምን ሰላይ እንደሚመድብ መስፈርቱ ምን እንደሆነና አንዳንዶቻችሁ ሃገር ጥላችሁ ለምን እንደወጣችሁ ስለምናውቅ እዚህ ተገኝታቸሁ የወያኔ ጭዳ ለምን አልሆናችሁም ለሚሏችሁ መለስ አትስጡ ፡፡

ይሄውላችሁ እኔ የምለው ቀላል ነው፡፡ እኔ ብቻ አይደለሁም ድፍን ኢትዮጵያ ቢጠየቅ የሚለው ይህንኑ ነው፡፡ እነዚህ በሰላማዊ መንገድ ይህንን መንግስት እንታገላለን የሚሉ ሃይሎች እንዴት እንደሚታገሉ ለምን አይነግሩንም፡፡ በተለይ በየግዜው ግንቦት ሰባትንና ሌላውን አምሮ የመለስን ግፈኛ አገዛዝ ለመታግል የቆረጠውን ተቃዋሚ ለመሳደብ የሚቀናቸው ግለሰቦች ለምንድን ነው መለስ ለሱዳን ያስረከበውን የሃገራችንን መሬት የክህደት ድርጊት በሚያገኙት መድረክ ሁሉ የማይኮንኑት፤ መቼ ነው ስለሚራበው ህዝብ፣ ስለኑሮ ውድነት ህዝብ ተቃወሞውን እንዲያሰማ በህገ መንግስት አለ የሚሉትን መብት ተጠቅመው ለተቃውሞ ሰልፍ የሚጠሩን፤ መቼ ነው ቴዲ የታሰረው ስለሃገሩ ስላዜመና ስለተቀኘ ነው ይፈታ የሚል ድምጻቸው የሚሰማው፤ መቼ ነው የምርጫ ቦርድ ገለልተኛ ሆኖ ይቋቋም፣ የፍትህ ስርአቱ ከፖለቲከኞች ቁጥጥር ውጭ ይደራጅ፤ በሃገሩ ህዝብ ሃብት የሚተዳደረው የኢትዮጵያ ቴሌቪዠንና ሬድዮ ለመለስ የቅጥፈት አፍ መሆኑ ቀርቶ ሁሉንም በነጻ ያገልግል የሚሉት፡፡ ምንድነው የመለሰን የለየለት አምባገነናዊ አገዛዝ ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ መታገያ እቅዳቸው?፡፡

ይህንን ሁሉ የምለው ለማሳጣት ፈልጌ አይደለም፡፡ ሁሉም ተቃዋሚ የሚያደርገው ተደምሮ የነጻነታችንን ቀን ያቀርባል ብዬ ከልቤ ስለማምን ነው፡፡ አብሬቸው ልቆም፣ ልሰልፍ፣ በገንዘቤ በእውቀቴ ልረዳቸው ስለምፈልግ ነው፡፡ ለምን ሌላውን ተቃዋሚ ለጠብ ከመጋበዝ የህዝብንም ስሜት ከመጉዳት፣ ከሁሉ መቅደም ያለበትን የራሳቸውን የትግል ታክቲክና ግብ በሚገባ ለህዝብ የማያስረዱት?። ይቻላል የሚሉትን ሰለማዊ ትግል አንዴት እንደሚቻል ለኛም ገልጸው፣ እኛም ከእነሱ ጎን እንድንቆም ለምን ያ ዋናው ስራቸው አይሆንም፡፡ ይህንን የምለው በቅርቡ አንድ ትልቅና ህዝብ ሲያከብራቸው የኖሩ ግለሰብ በአንድ በሃገር ቤት የታተመ ጋዜጣ ላይ የሰጡትን ቃለ መጠይቅ በማንበቤ ነው፡፡ ቃለ መጠይቁ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው አንድም ቦታ በስልጣን ላይ ስላለው፣ የሁላችንም መከራ ምንጭ ስለሆነው ግፈኛና ዘረኛ አገዛዝ ቃል አይተነፍስም፡፡ ጋዜጠኛዋም፣ ጥያቄ መላሹም አስቀድመው የተዘጋጁበት ይመስል በአገዛዙ ላይና ግለሰቡ በሃገራችን አለ በሚሉት ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ላይ ጥያቄ እንዳይነሳ ተደርጓል፡፡ ሰላማዊና ህጋዊ የሆነ ትንሽም ቢሆን የመታገያ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ካለ፣ ለምን አትሰበሰቡም ስትባሉ፣ ያውም ሁለት ፖሊሶች ተልከባችሁ፣ ወደ ገጽ 3 ዞሯል